በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፓርት

የካቲት 2008 ዓ.ም.

**አዲስ አበባ**

## ማውጫ

የካቲት 2008 ዓ.ም. ....... i
ማውጫ ....... i
ክፍል አንድ ....... 1
መግቢያ፤ ....... 1
የኤጀንሲው አመሰራረት፤ ....... 1
የኤጀንሲው ራዕይና ተልዕኮ ....... 2
የኤጀንሲው ዓላማ፣ሥልጣንና ተግባር ....... 2
የኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት፤ ....... 5
የፋይናንስ ምንጭ፡- ....... 5
የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ....... 7
የኦዲቱ አካባቢ ....... 7
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) እና የመመዘኛ መስፈርት ....... 7
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ....... 8
የሥራ ፍሰት መግለጫ (process description) ....... 9
ክፍል ሁለት ....... 11
ግኝቶች ....... 11
2.1 የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሚፈለገው ወቅት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ....... 11
የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መዘጋጀትን በተመለከተ ፤ ....... 11
የኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ ዕቅድና በጀት መዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ....... 12

የትኛው መድኃኒት እና ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ለመግዛት በየትኛው የግዥ ስልት ግዥ ሊከናወን እንደሚገባ በሚገልጽ መልኩ ዕቅድ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ........ 13

የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ እና የግዥው መንገድ የተመረጠበት ምክንያት መቀመጡን በተመለከተ፣ ........ 14

የፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያና የግዥ እቅድ አዘገጃጀት፣ ሥርጭትና የቴክኒክ ቡድን መቋቋሙን በተመለከተ፣ ........ 16

የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ምዝገባን በተመለከተ፣ ........ 17

ከእቅድ ውጪ ለሚፈጸም አስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ የሚያገለግል መስፈርት መዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ........ 18

በመንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ መፈጸሙን በተመለከተ፣ ........ 20

መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በግዥ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፣ ........ 21

ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸሙ ግዥዎችን የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ መቋቋሙን በተመለከተ፣ ........ 22

በከፍተኛ ገንዘብ የተፈጸሙ ግዥዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ሁኔታ በመረጃ መረብ (ድረ ገጽ) ላይ መቀመጡን በተመለከተ፣ ........ 23

በጥራት ጉድለት ስለተመለሱ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት ማስረጃዎቹ መድረሱን መተመለከተ፣ ........ 23

የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፣ ........ 25

ለኤጀንሲው ግዥን አስመልክቶ የሚሰጡትን ማሻሻያዎች ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 25

በጨረታ ላይ የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የጨረታን ውጤት በደብዳቤ መግለጹን በተመለከተ፤ ..... 26

2.2 በቀረበው ፍላጎትና ትእዛዝ መሰረት ከውጭ አገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲገዛላቸው ለጠየቁት አካላት መሰራጨታቸውን በተመለከተ፤ ..... 27

መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለጤና ተቋማት በወቅቱና በጠየቁት መጠን መድረሱን በተመለከተ፤ ..... 27

የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ..... 29

የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈባቸው (EXPIRED) መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በተመለከተ፤ ..... 30

ክፍል ሦስት ..... 33

መደምደሚያ ..... 33

ክፍል አራት ..... 35

የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 35

አባሪ አንድ፡ ..... 40

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ..... 40

አባሪ ሁለት፡ድርጅታዊ መዋቅር ..... 44

አባሪ ሦስት፡ ..... 45

በ2005፣ 2006 እና 2007 ዓ.ምግዥን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ እና የግዥው መንገድ የተመረጠበት ምክንያት በግልጽ ሳይቀመጥ የተገዙ መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን፤ ..... 45

አባሪ አራት፡ ..... 46

ለግል የጤና ተቋማት የተሰጡት መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን ..... 46

አባሪ አምስት ..... 47

*በናሙና ከታዩ አራት ቀጥታ ግዥዎች (ከአንድ አቅራቢ) ያለ ዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ የተፈጸሙ መድኃኒትና ህክምና መገልገያ ግዥዎች ዝርዝር*............................................................................. 47

**በአዲስ አበባ የሚገኙ የጤና ተቋማት ከመድኃኒት ፈንድ ውጭ የገዙት መድኃኒት በገንዘብ መጠን**......... 48

**አባሪ ሰባት፡** ........................................................................................................ 49

**በአዲስ አበባና በቅርንጫፍ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያበቃ መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን** ...................... 49

## ክፍል አንድ

### መግቢያ፤

1. ጤንነት ማለት የአካል የአእምሮ እና የማህበራዊ ደህንነት ደስተኛ ኑሮ ለመኖርና ከፍተኛ ምርታማነትን ለመቀዳጀት አስፈላጊ የሆነ ነው፡፡ከዚህም በመነሳት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ጤና ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፡፡ የጤና አገልግሎት እድገት ለሰብዓዊነት ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ግብአቶች አንዱ አካል ሆኖ የሚታይ ነው፡፡
2. ስለሆነም የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ በጤናው አገልግሎት ሥርዓት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስፈልጉና ደረጃቸውን የጠበቁ መድኃኒቶችን፣መሳሪያዎችን ዝርዝር ማዘጋጀትና ይህንንም ዝርዝር በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ፡፡ መድኃኒቶችን፣የክትባት መገልገያዎችን፣የሕክምና ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማጎልበት፣ለመፈብረክ ምርምር በማካሄድና በማልማት ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፣የምርቶች ግዢ፣ሥርጭት፣ክምችትና አጠቃቀም እንዲሻሻል ደረጃውን የጠበቀና ቀልጣፋ ሥርዓት በመፍጠር የምርቶችን ደህንነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር አቅምን ማጎልበት ተገቢ ነው፡፡
3. ይህንንም ለማሳካት የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ለመንግሥታዊ ጤና ተቋማት ጥራታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒትን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያቀርብ በአዋጅ ቁጥር 553/1999 ነሐሴ 29/1999 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡

### የኤጀንሲው አመሰራረት፤

4. የመድኃኒት ፈንድ እና አቅርቦት ኤጀንሲ አሁን የሚጠራበትን ስያሜና አደረጃጀት ከማግኘቱ በፊት በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራ ነበር፡፡
5. ይህም በ1939 ዓ.ም ዋናው መ/ቤት በመባል ይታወቅ ነበር፡፡በዚያን ግዜ ድርጅቱ ሲመሰረት ዓመታዊ ተንቀሳቃሽ የገንዘብ መጠኑ ከ80 ሚሊዮን ብር የሚዘል አልነበረም፡፡እንደገና በ1968 ዓ.ም የኢትዮጵያ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ድርጅት (ኢፋርሚኮር) በመባል ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን፣ የሰው የእንስሳ

እና የዕፅዋት መድኃኒቶችንና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማምረት እና ከውጭ በመግዛት ያከፋፍል ነበር፡፡

6. በ1986 የሽግግር መንግሥቱ የመድኃኒት ፖሊሲ በመቅረጽ በተደረገው የማደራጀት ሥራ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት (ፋርሚድ) በሚል ስያሜ እንደገና ተዋቀረ፡፡በዚህ ጊዜ በዓመት በአማካኝ 280 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያለው መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ያከፋፍል ነበር፡፡

7. በአዋጅ 553/1999 ዓ.ም አሁን በሚጠራበት የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ /መፈአኤ/ በሚል ስያሜ እንደገና እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ ኤጀንሲው ከታህሣሥ 2000 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ የጀመረ ሲሆን፤ በሁሉም የጤና ተቋማት ተደራሽነቱን ለማጠናከርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ይረዳው ዘንድ 17/አስራ ሰባት/ ቅርንጫፎችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል / ዋናው መ/ቤት፣ ደሴ፣ መቀሌ፣ ሀዋሳ፣ ድሬዳዋ፣ ጅማ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ነቀምት፣ አዳማ፣ አዲስ አበባ ቅርጫፍ እና ነገሌ ቦረና/ በመክፈት መድኃኒቶችንና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡በተጨማሪም አድማሱን በማስፋት በ2007 ዓ.ም ሰመራ፣ ቀብሪ ዳህር፣ ጋምቤላ፣ አርባምንጭ፣ ሽሬ እና አሶሳ ቅርጫፎችን እንዲከፈቱ አድርጓል፡፡

## የኤጀንሲው ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

8. "ጤናማና አምራች ሕብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት"፡፡

### ተልዕኮ

9. "የፋይናንስ አቅምን በማጎልበት በአግባቡ በመጠቀም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ፤ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልክ ለጤና ተቋማት ማቅረብ፣በየደረጃው የሚታየውን ብክነት ለማስወገድና አግባብ ያለው የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያስችል የማስፈፀም አቅምን መገንባት"፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ፣ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

10. የመንግሥት ጤና ተቋማት ጥራታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ እንዲያቀርቡ የማስቻል፤ የመድኃኒት አቅርቦቱን በማረጋገጥ የጤና አገልግሎቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ የማድረግ፤ፈንዱ ወጪውን እንዲሸፍን ከተደረገ በኃላ ተመልሶ በማዟዟር እራሱን በማሳደግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ተጠቀሱትን ዓላማዎችን እውን ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፡፡

**ሥልጣንና ተግባር**

11. በአዋጅ ቁጥር 553/1999 ለኤጀንሲው የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት፡-

- በመድኃኒት ፈንድ በመጠቀም በሀገሪቱ ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥራታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶችን በበቂ መጠን፣በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመንግሥታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥና የስርጭት ሥርዓት ይዘረጋል፣ይተገብራል፤
- ዘመናዊ የክምችት አስተዳደር ለማስፈን የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፣
- የክምችትና የሥርጭት አውታሮችን ፍትኃዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ ያስፋፋል፣ያጠናክራል፡፡
- አግባብ ባለው አካል ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን ለመንግሥት የጤና ተቋማት ያቀርባል፣አግባብ ሆኖ ሲገኝ በበቂ መጠን ሊቀርቡ ያልቻሉ የተመረጡ መድኃኒቶችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መንግሥታዊ ላልሆነና ለግል የጤና ተቋማት ያቀርባል፣
- የማጓጓዣ ሥርዓትን በማመቻቸት መድኃኒቶችን በቀጥታ ለወረዳዎች ሆስፒታሎችና እንደአመቺነቱ ለጤና ጣቢያዎች ያደርሳል፣
- በዘርፉ ከሚዘረጋው ስርዓት ጋር የሚጣጣም ዘመናዊ የሎጂስቲክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ይዘረጋል፣

- የአጭር፣የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የግዥ፣ የስርጭት፣ የማከማቸትና የማጓጓዝ ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገብራል፣አፈጻጸሙንም ይገመግማል፣
- በሚያከናውናቸው የስራ ዘርፎች ላይ ሙያዊ የምክር አገልግሎትና ሥልጠና ይሰጣል፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውን ይመራል፣ያስተባብራል፣
- ለሚሰጠው አገልግሎት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
- ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

12. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር፡-**

- ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል፤
- የኤጀንሲውን ስትራቴጂዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
- የኤጀንሲውን አመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያፀድቃል በሥራ ላይ መዋሉንም ክትትል በማድረግ ያረጋግጣል፤፤
- የመድኃኒት ፈንድን አሰባሰብና ከፈንዱም ላይ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ የሚሆንበትን የአሰራር ሥርዓት ያፀድቃል በሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
- የመድኃኒት ግዥ ክምችትና ሥርጭት አሰራር መመሪያዎችን ያፀድቃል በሥራ ላይ መዋላቸውንም ይከታተላል፤
- ኤጀንሲው ከባንክ የሚበደረውን የገንዘብ መጠንና አከፋፈሉን ይወስናል፤
- ለኤጀንሲው ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ምደባና ስንብት ያጸድቃል፡፡
- ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርት ያፀድቃል፤ የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖረት ይሰማል፤ በቀረበለት የኦዲት ሪፖርት ተመስርቶ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል ሪፖርቱንም ይፋ ያደርጋል፡፡
- ስለሚሸጡ ቋሚ ንብረቶችና ከመዝገብ የሚፋቁ ሂሣቦችን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ኮሚቴውን ይመራል፤ ያስተባብራል ኤጀንሲው የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ይወስናል፡፡

## የኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት፤

## ድርጅታዊ መዋቅር

13. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሆኖ አንድ ዋና ዳይሬክተር ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ዘጠኝ ዳይሬክቶሬቶች፣ አስራ አንድ ቅርንጫፎች እና አንድ ጽ/ቤት አሉት፡፡ (በአባሪ 2)

### የሰው ኃይል፤

14. ኤጀንሲው ለእነዚህ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በጥር 2008 በሥራ ላይ ያለ ወንድ 1241 እና ሴት 446 በድምሩ 1687 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት፡፡ ይህም በትምህርት ደረጃ ሲተነተን፣ ሁለተኛ ዲግሪ 37(2%)፣ የመጀመርያ ዲግሪ 412(24%)፣ ዲፕሎማ/ሰርተፍኬት 281(17%)፣ TVT/1-12 ክፍል፣ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ 957 (57%) ናቸው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ፡-

15. ኤጀንሲው የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እና በዕቅድ የያዛቸውን ስራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ምንጭ የሚያገኘው ከመድኃኒት አቅርቦት ከሚገኝ የተጣራ ገቢ ከመንግስት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ እና ከለጋሽ አካላት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ እርዳታ ሲሆን ፈንዱን ሲጠቀም የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን እንዲሸፍን ከተደረገ በኋላ ተመልሶ በማዟዟር ለመድኃኒት አገልግሎት ማስፋፊያና ማጠናከርያ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የኤጀንሲው የ2007 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈጻጸም ተጠይቆ ባለማቅረቡ የ2007 በጀት ዓመት የስድስት ወር አፈጻጸም ብቻ ነው የተካተተው፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል፡-

| ዓ.ም | የተመደ በጀት መጠን (000 ብር) | | | | ጠቅላላ ድምር | ጥቅም ላይ የዋለ መጠን (000 ብር) | | | | ቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለመድኃኒት ግዥ | | ለአስተዳደራዊ ሥራ | | | ለመድኃኒት ግዥ | | ለአስተዳደራዊ ሥራ | | |
| | መደበኛ | ፕሮግራም | መደበኛ | ካፒታል | | መደበኛ | ፕሮግራም | መደበኛ | ካፒታል | |
| 2005 | 2,400,000 | 3,600,000 | 127,000 | 425,000 | **6,552,000** | 2,227,951.00 | 3,472,049.00 | 126,922.00 | 376,245.00 | **6,203,167.00** |
| 2006 | 3,450,000 . | 4,811,000 | 181,000 | 413,000 | **8,855,000** | 2,999,098.00 | 2,999,758.52 | 183,464.95 | 269,268.97 | **6,628,590.40** |
| 2007 የ6 ወራት | 1,195,469 . | 2,389,351 | 192,628 | 262,654 | **4,040,102** | 1,095,722.73 | 1,095,722.73 | 92,817.46 | 31,005.74 | **3,222,947.52** |
| **ጠቅላላ ድምር** | 7,045,469 | 10,800,351 | 500,628 | 1,100,654 | 19,447,102 | 6,322,771.73 | 8,652,209.11 | 403,204.41 | 676,519.71 | 16,054,704.92 |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

16. የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና እንደዚሁም ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮችን መንስኤ በመለየት ለኤጀንሲው የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

17. ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

"የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) እና የመመዘኛ መስፈርት

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ

18. በተለየው የኦዲት ካባቢ (audit area) ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል እነሱም፡-

1. መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች፣ በሚፈለገው ወቅት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
2. በቀረበው ፍላጎትና ትእዛዝ መሰረት ከውጭ አገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች እና የሕክምና መሣሪያዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲገዛላቸው ለጠየቁት አካላት መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ

የሚሉት ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣

19. ከላይ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመገምገም የሚያስችል 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅቷል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡) በመመዘኛ

መስፈርቱም ላይ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተልኮላቸው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2005-2007 ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት እና የ2008 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

21. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የኤጀንሲውን አሠራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ ሠነዶችና ማስረጃዎችን (የተለያዩ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የጥናት ሪፖርቶች፣ የየአመቱን ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ የስትራቴጅክ ዕቅድ)፣ የቦርድ ቃለ ጉባዔ፣ የሥራ አመራር (የማናጅመንት) ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ኤጀንሲውን በሚመለከት የወጡ የተለያዩ ብሮሸሮች ጋዜጦችና የተለያዩ መመሪያዎችን የከለሰ ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የኤጀንሲውን እና አዲስ አበባ የሚገኘውን የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች አነጋግሯል፡፡ በኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ጊቢ ውስጥ የሚገኙ 4 መጋዘኖችን፣ እና በሽጎሌ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን፣ በድምሩ አምስት የኤጀንሲው እና በሳሪስ በእርሻ ሰብል ግቢ ውስጥ የሚገኙ 3 የኪራይ መጋዘኖችን በናሙና መርጦ በመጎብኘት ለመጋዘን ኃላፊዎችም መጠይቅ አቅርቧል፡፡

22. በተጨማሪም አዲስ አበባ ከሚገኙ የመንግሥት ሆስፒታሎች ውስጥ በናሙና በተመረጡ አስር ሆስፒታሎች የመድኃኒት ግዥና አቅርቦትን በሚመለከት መረጃዎችን፣ በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የመድኃኒት ጥራት ቁጥጥርና የመጠቀሚያ ጊዜን፣የማስቀመጫ መጋዘኖችን በሚመለከት መመሪያዎችና ደንቦችን፣ በአዲስ አበባ ከሚገኙ በናሙና ለተመረጡ አራት የመድኃኒትና ኬሚካል አምራቾች ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች መጠይቅ በማቅረብና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡

## የሥራ ፍሰት መግለጫ (process description)

23. **የግዥ ትንበያ እና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት**

- የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ከጤና ተቋማት የሚቀርብ የመድኃኒት ጥያቄ መረጃ መያዝ፤

⇩

- በማዕከል የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል መወሰን፤

⇩

- የጤና ፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያና የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት፤መወሰን፤

⇩

- የመድኃኒት ክምችት አስተዳደርና የክምችት መጠን ማመላከት፤

⇩

የተመረጡ መድኃኒቶች (vital Drugs and Related Supplies) አቅርቦት ክትትል ማድረግ፤

⇩

- እና የሌሎች መድኃኒቶች የክምችት መጠን መከታተል፤

24. <u>የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ግዥ ዳይሬክቶሬ</u> የሥራ ፍሰት መግለጫ (process description)

የመንግሥት ሕክምና መስጫ ተቋማት ለቀጣይ ዓመት የሚያስፈልጋቸውን የመድኃኒት ግዥ መጠይቅ በአከባቢያቸው ላለው የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ማቅረብ፤

⇩

- የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዲሁም በግል አስመጪዎች ሊሟላ ያልቻለውን የመድኃኒት ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት በየአመቱ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያዎች ግዥ ፍላጎታቸውን ለግዥ ትንበያና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ፤

⇩

- የግዥ ትንበያና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በኤጀንሲው የሚገኙ መጋዘኖች ያላቸውን ክምችት፣ ግዥ ተከናውኖባቸው በመንገድ ላይ የሚገኙትን ግምት ውስጥ በመከተት

በበጀት አመቱ ሊገዙ የሚገቡ መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በምን ያህል ዋጋ፣ መቼ መጋዘን መድረስ እንደሚገባቸው እና ምን ያህል መጠን መገዛት እንደሚገባው በመተንበይ ወይም በማቀድ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ለውሳኔ ማቅረብ፣

⇩

- የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርም ያለውን በጀት በማየት ውሳኔ ማስተላለፍ፣

⇩

- በውሳኔው መሰረትም ግዥ እንዲከናወንባቸው ለግዥ ዳይሬክቶሬት መላክ፣

⇩

- የግዥ ዳይሬክቶሬትም መድኃቶቹን ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ለመግዛት የሚያስችል ዘዴ በመምረጥ ለውሳኔ ለምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እና ለዋና ዳይሬክተሩ በቅደም ተከተል ማቅረብ፣

⇩

- ዋናው ዳይሬክተር በሚያስተላልፈው ውሳኔ መሰረትም ግዥውን ማከናወን፣

⇩

- ግዥ የተከናወነበት መድኃኒት በዕቅዱ እና በመርሃ ግብሩ መሠረት የኤጀንሲው መጋዘን ውስጥ ገቢ እንዲደረግ ክትትል በማድረግ መጋዘን እንዲገባ ማድረግ

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

## 2.1 የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሚፈለገው ወቅት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

### የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መዘጋጀትን በተመለከተ ፤

25. የኤጀንሲው የግዥ መመሪያ ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅና ሥራ ላይ እንዲውል ሊደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የግዥ ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ የካቲት 2005 ዓ.ም. አቅርቦ ነበር፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ የቀረበው ረቂቅ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ከመንግሥት ግዥ አዋጅና መመሪያ ጋር የማይጋጭ መሆኑን በመመሪያው ላይ እንዲጠቀስ፣ በሚወጡ የግዥ ጨረታዎች የሚሳተፉ አቅራቢዎች ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን እንዲሁም ከፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚሰጥ ዝርዝር እንደሚጠቀም፣ በግልጽ እንዲቀመጡ የሚል ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲጸድቅ ቢወስንም በቦርዱ የተሰጡት ማስተካከያዎች ሳይካተቱ ሰኔ 4 ቀን 2005 ዓ.ም. መጽደቁ ታውቋል፡፡

27. በተጨማሪም በኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ኤጀንሲው የሚያወጣው የግዥ መመሪያ የመንግሥት የግዥ መርሆዎችን ይከተላል ብሎ በግልጽ የደነገገ እና የግዥ አዋጁም ተፈጻሚነት በሁሉም በፌዴራል መንግሥት ግዥዎች ላይ ተግባራዊ እንደሚሆን ይገልጻል፡፡ ከመንግሥት ግዥ ድንጋጌዎች መካከል በአዋጁ በተፈቀደው መሰረት ሁሉም ግዥዎች በግልጽ ጨረታ መፈጸም እንዳለበት እና ለሌሎቹ ግዥዎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለእያንዳንዱ የግዥ ዘዴ መፈጸም ያለበትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በመመሪያ እንዲቀመጥ ደንግጓል፡፡ ነገር ግን የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የግዥ አዋጁ ላይ የተገለጹትን 49/2፣ 51/2፣52/2 እና 55 አንቀጾች በግልጽ በሚጻረር

መልክ መመሪያው በተለያየ ግዥ ስልት ለሚፈጸሙ ግዥዎች የገንዘብ መጠን ጣሪያ እንደማያስፈልገው ይገልጻል፡፡

28. የኤጀንሲው ኃላፊዎች የተዘጋጀው ረቂቅ የግዥ መመሪያ በሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔ መሰረት ለምን እንዳልተስተካከለ እና ከግዥ አዋጁ ጋር ለምን እንዲጣጣም እንዳልተደረገ ተጠይቀው ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

29. ኤጀንሲው የግዥ መመሪያውን የሥራ አመራር ቦርድ በአስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት አለማስተካከሉና የመንግሥት የግዥ አዋጅና መመሪያን መሰረት በማድረግ በየግዥ ስልቱ የገንዘብ መጠን ጣራ እንዲቀመጥ አለመደረጉ ለህገወጥ አሠራርና ለምዝበራ በር ይከፍታል፡፡

## የኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ ዕቅድና በጀት መዘጋጀቱን በተመለከተ፣

30. ኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ እቅድ ከባለድርሻ አካላት ፍላጎታቸውን በማሰባሰብ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ መድኃኒት በኤጀንሲው እንዲገዛላቸው የሚፈልጉ ማናቸውም አካላት ፍላጎታቸውን በበጀት አስደግፈው ሊያቀርቡና ኤጀንሲውም በበጀት መደገፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ኤጀንሲው በየዓመቱ የሚያዘጋጀውን የግዥ ዕቅድ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ እና የጸደቀውም በዕቅዱ መሰረት በትክክል በሥራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ ከጤና ቢሮዎችና ከጤና ተቋማት በየዓመቱ የሚሰበስብ ቢሆንም ፍላጎቶቹ በበጀት የተደገፉ መሆናቸውን ግን እንደማያረጋግጥ፣ የተሰበሰበውን ዓመታዊ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት ጥያቄ በመጠን፣ በጊዜና እና በገንዘብ በመተንተን በቀረበው ፍላጎት መሰረት የመድኃኒት ግዢ እቅድ እንዲዘጋጅ እንዳልተደረገ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው የሚፈጽማቸው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ በየበጀት ዓመቱ ለሚመለከተው አካል አቀርቦ እንዲጸድቅና እንዲፈቀድ ስለመደረጉ እና የተዘጋጀውም ዕቅድ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 22/2 መሠረት ዕቅዱ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለመላኩ መረጃ አልቀረበም፡፡ የተፈቀደውም በትክክል ሥራ ላይ የዋለ ለመሆኑ ክትትል የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለ ጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው ዓመታዊ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ትንበያና ግዥ ዕቅድ በዝርዝር ከተዘጋጀ በኋላ በጥቅል የበጀት እና የዓመታዊ ዕቅድ አካል ሆኖ ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ እንደሚጸድቅ፣ ኤጀንሲው የሚያከናውነው አብዛኛው ግዥ የጤና ፕሮግራሞች ግብዓት እንደመሆኑ የግዥ ዕቅዱ የፕሮጀክት ስምምነት አካል ሆኖ እንደሚጸድቅ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ በተመረጡ መድኃኒቶች ላይ የማዕቀፍ ግዥ ለማከናወን በዕቅድ መያዛቸውን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ቢሉም ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ጸድቋል የተባለው የግዥ ዕቅድ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ መቀበል ያስቸግራል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያ የግዥ ዕቅድ ነው በማለት የቀረበው ሰነድ በተለያዩ ጊዜ የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያ ግዢ እንዲፈጸም ለሚቀርብ ጥያቄ የተዘጋጀ የቢሮ ማስታወሻ በመሆኑ የየበጀት ዓመቱን ጠቅላላ የበጀትና የግዥ እቅድ የሚያሳይ ስላልሆነ የኤጀንሲው የግዥ ዕቅድ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

33. ኤጀንሲው ባልተዘጋጀ፣ ባልተፈቀደና ክትትል በማይደረግበት እቅድና በጀት በዓመት ቢሊዮኖች በሚቆጠር ብር ከአገር ውስጥም ከውጭም ሀገር ግዥን ማከናወን የመንግሥት ሀብት ያላግባብ እንዲባክንና መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች፣ በሚፈለገው ወቅት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥ ስርዓት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

**የትኛው መድኃኒት እና ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ለመግዛት በየትኛው የግዥ ስልት ግዥ ሊከናወን እንደሚገባ በሚገልጽ መልኩ ዕቅድ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

34. ኤጀንሲው ለሚያከናውናቸው የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥዎች የትኛው መድኃኒት ወይም የሕክምና መገልገያ መሣሪያ በየትኛው የግዥ ስልት (በግልጽ ጨረታ፣ ውስን ጨረታ፣ ከአንድ አቅራቢ፣ በዋጋ ማወዳደሪያ) ግዥዎች ሊከናወኑ እንደሚገባ በሚገልጽ መልኩ ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሸፈናቸው ከ2005-2007 ባሉት የበጀት ዓመታት በናሙና ተመርጠው ከተከለሱ የግዥ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በኤጀንሲው የተከናወኑ

የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ከመፈጸሙ በፊት ግዥው ሰለሚከናወንበት የግዥ ስልት ዕቅድ በግዥና ንበረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/ 2001 አንቀጽ 22 እና በግዥ መመሪያ አንቀጽ 10፣ 12 እና 15 መሰረት ያልተዘጋጀ እና በታቀደው መሰረት የተፈጸመ ግዥ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

36. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ዘዴ በገንዘብ መጠን ጣሪያ ሳይሆን በኤጀንሲው የግዥ መመሪያ መስፈርት መሠረት የተፈጸመ ነው በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 32/2 እና የግዥ መመሪያ አንቀጽ 18 በግልጽ የተደነገገውን በመመሪያ መሻር ስለማይቻል የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

37. በመሆኑም በመንግሥት የግዥ አዋጅ እና የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የማይከናወን ግዥ የመንግሥትን ገንዘብ በቁጠባ ሥራ ላይ እንዳይውል፤ መድኃኒት እና የህክምና መሳሪያዎች በፍጥነት፣ በጥራት እንደዚሁም በጊዜ፤ እንዲቀርቡ የማያደርግ እና ለሕገወጥ አሰራርና ለምዝበራ በር እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

## የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ እና የግዥው መንገድ የተመረጠበት ምክንያት መቀመጡን በተመለከተ፤

38. የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያ ግዥ ሲከናወን የግዥውን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ ሊያያዝ ይገባል፡፡ ግዥው ሲፈጸም የግዥው መንገድ የተመረጠበት ግልጽ ምክንያት ተገልጾ እንዲቀመጥ ሊደረግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተከለሱት ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ከ2005 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ በኤጀንሲው፤

- በውስን ጨረታ ከአገር ውስጥ በብር 4,193,427,553.44 ከዓለም አቀፍ በብር 7,173,956,810.36፤ በድምሩ በብር 11,367,384,363.80፤ በግልጽ ጨረታ፤ ከዓለም አቀፍ በብር 4,368,853,710.36፣ በቀጥታ ግዥ(ከአንድ አቅራቢ) ከአገር ውስጥ በብር 42,435,535.86 ከዓለም አቀፍ በብር 649,783,580.60 በድምሩ በብር 692,219,116.46፤በዋጋ ማቅረቢያ (በለቀማ ግዥ) ከዓለም አቀፍ በብር 188,167,810.44፤ ከአገር ውስጥ በብር 26,488,341.55 በድምሩ በብር 214,656,152.00 በአጠቃላይ ድምር ብር 16,643,113,342.61(አስራ ስድስት

ቢሊየን ስድስት መቶ አርባ ሦስት ሚሊየን አንድ መቶ አስራ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ሁለት ከ61/100)

ለተፈጸመ የመድኃኒት ግዥ የግዥውን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ እና፤ የግዥው መንገድ የተመረጠበት ግልጽ ምክንያት (ከፍላጎት ጥያቄ ጀምሮ የወጣውን የጥሪ ማስታወቂያ፤ መስፈረቱን፤ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት ማስረጃና የመወዳደሪያ የገንዘብ መጠን፤የጨረታ ኮሚቴ ኃሳብ፤ የመሳሰሉት ማስረጃዎች) ተሟልተው ግዥ ስለመከናወኑ መረጃው እንዲቀርብ ወይም ካልተዘጋጀ ምክንያቱን እንዲያስረዱ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በተደጋጋሚ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አላቀረቡም፡፡ (በየአመቱ የተፈጸመው ግዥ በአባሪ 3 ላይ ተያይዟል፡፡)

40. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ሁሉም ግዥዎች በቦርዱ በፀደቀው የኤጀንሲው መመሪያ መሠረት የግዥ ስልት እየተመረጠ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ፀድቆ የሚከናወን በመሆኑ ይህንንም ከሰነድ ማረጋገጥ ይቻላል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የግዥውን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ የግዥው መንገድ የተመረጠበት ግልጽ ምክንያት (ከፍላጎት ጥያቄ ጀምሮ የወጣውን የጥሪ ማስታወቂያ፤መስፈርቱን፤ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት ማስረጃና የመወዳደሪያ የገንዘብ መጠን፣ የጨረታ ኮሚቴ ኃሳብ፤ የመሳሰሉት ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው እነዚህ መረጃዎች መያዝ እንዳለባቸው በመንግሥት የግዥ አዋጅ ቁጥር 449/2001 አንቀጽ 23፣ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 15፣ እና የኤጀንሲው የግዥ መመሪያ ጭምር የሚያስገድድ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

41. በመንግሥት የግዥ አዋጅ መሰረት ለማንኛውም ግዥ ሂደቱን የሚገልጽ ማስረጃዎች በቅደም ተከተላቸው ፋይል ተደርገው እንዲቀመጡ ካልተደረገ የተፈጸመው ግዥ ትክክለኛና ሂደቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ የማይቻል እና ኤጀንሲው የሚፈጸመው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ግዥ ህግንና ደንብን የተከተለ ለመሆኑ ማረጋገጥን አዳጋች በማድረግ ግዥው ለምዝበራና ለብክነት የተጋለጠ እንዲሆን በር ይከፍታል፡፡

**የፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያና የግዥ እቅድ አዘገጃጀት፣ ሥርጭትና የቴክኒክ ቡድን መቋቋሙን በተመለከተ፤**

42. በጤና ፕሮግራም በጀት ለሚገዙ (የኤች.አይ.ቪ. (HIV)፣ የጸረ ወባ፤ የቤተሰብ ምጣኔ፤ የሳንባ ነቀርሳ (የቲቢና) የሥጋ ደዌ (ሌፐረሲ) እንዲሁም ሌሎች የፕሮግራም መድኃኒቶች) ትንበያና የግዥ እቅድ አዘገጃጀትን ለማከናወን የቴክኒክ ቡድን እንዲቋቋም ሊደረግ እና በቀረበው ፍላጎት መሰረት ግዥ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በዕቅዱም መሰረት ለሚገዙ መድኃኒቶች በጀት እንዲያዝና የተገዙትም መድኃኒቶች ለየጤና ተቋማቱ እንዲዳረሱ ሊደረግ ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መድኃኒቶች ግዥ በስተቀር ለሌሎቹ የፕሮግራም ግዥዎች የቴክኒክ ቡድኑ አለመቋቋሙ፣ ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ እና ከወባ መድኃኒቶች በስተቀር በየአመቱ የሦስት ዓመት ፍላጎትና የአንድ ዓመት የግዥ እቅድ እንደየፕሮግራሙ ተጨባጭ ሁኔታ እንዲዘጋጅ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከ2005 -2007 ድረስ በጤና ፕሮግራም ለሚገዙ መድኃኒቶች ምን ያህል በጀት ተይዞ እንደነበር የሚገልጽ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡ በጤና ፕሮግራም መድኃኒቶች ተብለው የተገዙ መድኃኒቶችም በሚፈለግበት ወቅትና መጠን ለየጤና ተቋማቱ እንደማይደርሳቸው በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ አዲስ አበባ የሚገኙ የጤና ተቋማት ከቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

44. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ፣ የወባ፣ የቲቢና የሌሎችም ፕሮግራሞች የ3 ዓመት ፍላጎት ትንበያ ይከናወናል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መድኃኒቶች በስተቀር ለሌሎቹ የፕሮግራም (የቤተሰብ ምጣኔ፤ የሳንባ ነቀርሳ (የቲቢና) የሥጋ ደዌ (ሌፐረሲ) መድኃኒቶች የግዥ ዕቅድና ትንበያ እንዲሁም ሌሎች የፕሮግራም መድኃኒቶች) የቴክኒክ ቡድን እንዲቋቋም ስለመደረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

45. ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻቸው የጤና ፕሮግራም መድኃኒቶችን ባልተዘጋጀ ፍላጎትና ባልታቀደ ሁኔታ በልምድ እንዲገዙ ማድረግ መድኃኒቶቹ ባልተፈለገ ጊዜ ተገዝተው ጥቅም ላይ ሳይውሉ እንዲባክኑ፣ በበቂ ሁኔታ ሳይገዙ ቀርተው እጥረት እንዲከሰት ሊያደርግ፣ የተገዙ መድኃኒቶችም ለተጠቃሚዎች በወቅቱ አለመሰራጨታቸው

በተጠቃሚው ላይ እጥረት እንዲፈጠርና ከፍተኛ የጤና ጉዳት እንዲደርስ ከማድረጉም በላይ ለዚህ ፕሮግራም የሚውል እርዳታንም ጭምር ለወደፊቱ እንዳይቀጥል የሚያደርግ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

**የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ምዝገባን በተመለከተ፤**

46. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ምዝገባ በጊዜ፣ በአይነት፣ በመጠን፣ በገንዘብ እና ለማን እና ከየትኛው በጀት እንደተገዛ በሚያሳይ መልክ ተዘርዝሮ ሊመዘገብ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተገዙ መድኃኒቶች መቼ፣ ለማን፣ እና ከየትኛው በጀት እንደተገዙ የሚያሳይ ግልጽ ምዝገባ እንደሌለ ታውቋል፡፡

48. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ምዝገባ ከተከናወነ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ካልተከናወነም ያልተከናወነበት ምክንያት በተደጋጋሚ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ ሆነ ምክንያቱን አላቀረቡም፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሀገር ውስጥ ወኪሎች ለመንግሥት ሊገኝ የሚገባውን ግብር ለማገዝ ይረዳ ዘንድ ከ500 ገጽ በላይ ሰነድ ተዘጋጅቶ ተልኳል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየት ቢሰጡም ለኦዲቱ እንዲቀርብ የተጠየቀው ኤጀንሲ ያከናወናቸውን የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ግዥን የሚያሳይ ምዝገባን እንጂ የመድኃኒት አቅራቢዎች የሀብትና እዳ ማሳወቂያ ስላልሆነ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

49. ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶበት የሚፈጸም የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥዎችን ዝርዝር ምዝገባ አለማከናወን ግዥዎቹ የተከናወኑላቸው አካላት በትክክል እና በወቅቱ እንዳያደርሷቸው ወይንም ለማን እንደተገዙ ሳይታወቅ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሊያልፍ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ከግዥ ጋር የተያያዘ ሂሳብ ኦዲት እንዳይደረግ፣ ትክክለኛ ዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንዳይቀርብና የኤጀንሲው የፈንድ ሂሳብ እንቅስቃሴን ለመረዳት አዳጋች የሚያደርግ ይሆናል፡፡

**ከእቅድ ውጪ ለሚፈጸም አስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ የሚያገለግል መስፈርት መዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

50. ኤጀንሲው አስቸኳይ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት ከእቅድ ውጪ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚመራበት የአስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸም መስፈርት ሊያዘጋጅ እና በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ከእቅድ ውጪ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚመራበት የአስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸም መስፈርት እንዳላዘጋጀ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የአስቸኳይ ግዥዎች ውስጥ፤ መስፈርት ሳይኖር በቁጥር 31/15፤ 32/15፤ 26/15/29/15፤ 21/15፤ 0/15፤33/15፤ 30/15 በተመዘገቡ ግዥዎች ኤጀንሲው በድምሩ ብር 16,863,333.00 (አስራ ስድስት ሚሊየን ስምንት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት) ብር የሚያወጡ የአስቸኳይ የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪዎች ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

52. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች መስፈርቱ ለምን እንዳልተዘጋጀና በምን መስፈርት የአስቸኳይ ግዥዎች እንደፈጸሙ ተጠይቀው ሁሉም ግዥዎች አስቸኳይ ስለሆኑ በጥያቄ የተገዙ ናቸው ለዚህም ደጋፊ ማስረጃ አለን በማለት አቅርበዋል፡፡ ግዥዎቹ አስቸኳይ ስለመሆናቸው ከቀረቡት ማስረጃዎች ውስጥ በግዥ ቁጥር 33/15 የአስቸኳዩ አሳሳቢነት ተገልጾ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቁጥር መጠ/17/14/29 በቀን 15/ 2/08 ጠያቂነት የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ በበውሃ እጥረት ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች መከሰት በጀመረው የአከክ ወረርሽኝ ወደ ሌላ አካበቢ እንዳይዛመት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የአሰቸኳይ መድኃኒት ግዥ እንዲከናወንለት በጠየቀው መሰረት ከተከናወነው ግዥ በስተቀር፡-

- በግዥ ቁጥር 26/15 Propylthiourlacil 100mg scored tablet ክምችት እየሳሳ በመምጣቱ ግዥ ለማከናወን እና መድኃኒቱ ህይወት አድን በመሆኑ በአስቸኳይ መድኃኒቱ በብር 4,248,323.06 እንዲገዛ መደረጉን ኃላፊዎቹ ቢገልጹም የአነስተኛ የክምችት አሥተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት በመደበኛ የግዥ ሥርዓት መገዛት ይችል ስለነበረ እንዲሁም ይህ መድኃኒት መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ተገዝቶ የገባ እና በድጋሚ በአስቸኳይ ግዥ የተጠየቀው ደግሞ በግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ.ም. በመሆኑ

መጀመሪያም የመጋቢቱ ግዥ ሲፈጸም የመድኃኒቱ ህይወት አድንነት ከግምት ውስጥ መግባት በበቂ መጠን መገዛት የነበረበት ስልሆነ ግዥው አስቸኳይ ነው የተባለውን አልተቀበልነውም፡፡

- በግዥ ቁጥር 21/15 ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለካንሰር ህክምና አገልግሎት ማስፋፊያ የሚውሉ መድኃኒቶች በኤም.ዲ.ጂ.ፒ.ኤፍ. (MDGPF) በጀት ዕቅድ የሚገዙ መድኃኒቶች ብር 4,791,512.65 በአለምአቀፍ ጨረታና በውስን ጨረታ ወጥቶ አቅራቢ በመጥፋቱ በዋጋ ማወዳደሪያ /በአለምአቀፍ ሾፒንግ /በአስቸኳይ የተገዛ መሆኑን ኃላፊዎቹ ቢገልጹም በሕጉ መሰረት በተደጋጋሚ ጨረታ ስለመውጣቱ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣ የካንሰር መድኃኒት በአስቸኳይ ይገዛ ብሎ የጠየቀበት ማስረጃ አለመቅረቡ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የካንሰር መድኃኒቶች በአስቸኳይ እንዲገዙለት የተጠየቀው በቁጥር ጥቁ 2/1/15/3651/07 በግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ሲሆን ጨረታ ወጥቶ አቅራቢ ስላልተገኘላቸው በግዥ ማወዳደሪያ ይገዙ ተብሎ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሀሳብ የቀረበው ግንቦት 14 ቀን 2007 መሆኑ፣ በድጋሚ ለመድኃኒቶቹ ግዥ ጨረታ እንዲወጣ በሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም. ለኤጀንሲው የኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ጥያቄ መቅረቡ፣ የቀረቡት ማስረጃዎች እርስ በእርስ የሚቃረኑ ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡
- በግዥ ቁጥር 31/15 የተፈጸመ ለብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት አስቸኳይ የኮፐር ሰልፌት (Copper selphate) በአለም አቀፍ ጨረታ ላይ ተጫራች ያልቀረበ በመሆኑ አስቸኳይ የአገር ውስጥ ግዥ እንዲፈጸም ነሐሴ 14 ቀን 2007 በደብዳቤ ስለጠየቀ የተገዛ ነው በማለት የኤጀንሲው ኃላፊዎች ሰነድ ቢያቀርቡም መድኃኒቱ የግዥ ምዘናው እራሱ ገና የተጠናቀቀው ጥቅምት 9 ቀን 2008 ዓ.ም. በመሆኑ፣ ግዥው አስቸኳይ ከነበረ እና መድኃኒቱ በአገር ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ለምን በመጀመሪያ የአለም አቀፍ ጨረታ ማውጣት እንዳስፈለገ መረጃው ስላልቀረበ የግዥው አስቸኳይነትን ለመቀበል አዳጋች ከማድረጉም በላይ ከዚህ በፊት ወጣ የተባለው የአለም አቀፍ ጨረታ እና የጨረታው ሂደት ማስረጃ ለኦዲቱ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡
- በተጨማሪም ለግዥ ቁጥሮች 10/15፣ 29/15፣ 30/15፣ እና 32/15 የግዥዎቹን አስቸኳይነት የሚገልጽ ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

53. በተጨማሪም የተጠቀሱትን አስቸኳይ የተባሉት ግዥዎችን ለመፈጸም ምን መስፈረት እንደተጠቀሙ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

54. ከእቅድ ውጭ ለሚያጋጥሙ አስቸኳይ ግዥዎች ሊያጋጥሙና ሊከሰቱ የሚችልበት አጋጣሚ ቢኖርም ያለመመሪያና ያለእቅድ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያወጣ አስቸኳይ ግዥ መፈጸም ኤጀንሲውን ያለእቅድ እንዲመራና የሚገዙትም መድኃኒቶች ትክለኛውን የግዥ መመሪያና ደንብን ባልተከተለ መንገድ እንዲከናወኑ በማድረግ ለህገወጥ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

**በመንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ መፈጸሙን በተመለከተ፤**

55. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን የመድኃኒትም ሆነ የህክምና መገልገያ መሣሪዎች ግዥዎችን በመንግሥት የግዥ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ሊያከናውን ይገባል፡፡

56. በየግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 32/2 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መንግሥት የግዥ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት የገንዘብ መጠናቸው ለግንባታ ዘርፍ ከብር 50,000,000.00 በላይ፣ ለዕቃ ግዥ ከብር 10,000,000.00 በላይ፣ ለምክር አገልግሎት ከብር 2,500,000.00 በላይ እና ለአገልግሎቶች ግዥ ከብር 7,000,000.00 በላይ የሆኑ ግዥዎች በሙሉ በግልጽ ጨረታ በማውጣት መከናወን የሚገባ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ኦዲቱ በተከናወነባቸው በጀት ዓመታት ከ2005-2007 ባለው ጊዜ በናሙና ተመርጠው በታዩ ግዥዎች ለመግዛት ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ባላይ፤

- በውስን ጨረታ ከአገር ውስጥ የብር 4,193,427,553.44 ከአለም አቀፍ የብር 7,173,956,810.36፣ በድምሩ ብር 11,367,384,363.80
- በቀጥታ ግዥ (ከአንድ አቅራቢ)፤ ከአገር ውስጥ የብር 42,435,535.86 ከአለም አቀፍ የብር 649,783,580.60 በድምሩ በብር 692,219,116.46 እና
- በፕሮፎርማ (በዋጋ ማቅረቢያ) ግዥ ከአገር ውስጥ 26,488,341.55 ከአለም አቀፍ የብር 188,167,810.44 በድምሩ በብር 214,656,151.99

በጠቅላላ ድምር የብር 12,274,259,632.25 (አስራ ሁለት ቢሊየን ሁለት መቶ ሰባ አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር ከ25/100) የሚያወጣ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ (የየአመቱን ዝርዝር በአባሪ ሦስት ላይ ተያይዟል)

57. ከመንግሥት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ግዥዎች ለምን እንደተከናወኑ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው ኤጀንሲው በተለያዩ የግዥ ዘዴዎችን የሚፈጽመው በገንዘብ መጠን ጣሪያ እንዳይሆን በፀደቀው የኤጀንሲው ግዥ መመሪያ መሠረት የተፈጸመ ነው በማለት በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መመሪያው የመንግሥት ግዥ አዋጅ 649/2001 መሰረትን አድርጎ እንዲስተካከል የስራ አመራር ቦርዱ የሰጠውን የማተካከያ ሃሳብ ሳያካትት ተግባራዊ የተደረገ የግዥ መመሪያ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

58. ግዥዎችን በተቀመጠው የአገሪቱ የግዥ ህግ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት አለማከናወን ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እና የመንግሥት ሀብትን ለህገወጥ አሰራር፣ ምዝበራና ለብክነት ከማጋለጡም በላይ ከጥቅል ግዥ የሚገኘውን ጥቅም ያሳጣል፡፡

**መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በግዥ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፤**

59. ኤጀንሲው መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ በግዥ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ በማውጣት በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

60. በኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በበቂ መጠን ሊቀርቡ ያልቻሉ መድኃኒቶችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መንግሥታዊ ላልሆኑ እና ለግል ጤና ተቋማት መድኃኒቶችን ኤጀንሲው እንደሚያቀርብ ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው መመሪያ ሳይኖር ከ2005-2007 ባለው በጀት ዓመት ብር 245,376,945.72 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሚሊየን ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ከ72/100) የሚያወጡ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት የተከፋፈለ መሆኑ ከኤጀንሲው ቅርንጫፎች ከቀረበ ሪፖርት ታውቋል፤ (አባሪ አራት)

61. የኤጀንሲው ኃላፊዎች በምን መስፈርት እንደተከፋፈለ ተጠይቀው በግሉ ዘርፍ በመድኃኒትና የህክምና መገልገያ ጅምላ አከፋፋዮች የማይቀርቡ ህይወት አድን መድኃኒቶች ለግሉ ዘርፍ የአቅርቦት ክፍተት የተነሳ በግሉ ዘርፍ ጤና ተቋማት አገልግሎት እንዳይቋረጥ ይሰጥ እንደነበር፣ ለወደፊቱ መመሪያ ተዘጋጅቶ በቦርዱ እንዲፀድቅ እንደሚደረግ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

62. የአሰራር መመሪያ ሳይኖር እና በዕቅድ ሳይያዝ ሌሎች በዕቅድ እንዲገዛላቸው የጠየቁትን መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለግል የጤና ተቋማት እንዲከፋፈል ማድረግ ትክክል ካለመሆኑም በላይ ለህገወጥ አሰራር ምቹ በር ይከፍታል፡፡

**ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸሙ ግዥዎችን የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ መቋቋሙን በተመለከተ፤**

63. ኤጀንሲው ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ የድርድር ማድረጊያ አትኩረት- ነጥቦች በግዥ አዋጁ አንቀጽ 52/2 መሰረት ሊያዘጋጅ እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በማጸደቅ ለተደራዳሪ ወገኖች ሊሰጥ ይገባል፡፡በተጨማሪም ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸሙ ግዥዎች የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ በማቋቋም የዋጋ ድርድር ሊያደረግ ይገባል፡፡

64. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት በቁጥር 21/13፣ 01/14፣ 05/15፣ 34/15 በተመዘገቡ ግዥዎች ከድስት አቅራቢዎች በ2005፣ 2006 እና 2007 ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸሙ ግዥዎች የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ በማቋቋም ድርድር ሳይደረግ እንዲሁም በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 52/2 መሰረት ድርድር የማድረጊያ አትኩረት-ነጥቦች ተዘጋጅተው ለተደራዳሪዎቹ ሳይሰጥ የብር 21,250,689.83 (ሀያ አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከ83/100) በግዥ አዋጁ ሆነ በግዥ መመሪያው ላይ የተደነገጉት ሳይሟሉ የመድኃኒትና የህክምና መሣሪያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡ (አባሪ አምስት)

65. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ድርድር የማድረጊያ አትኩረተ-ነጥቦች ተዘጋጅተው ለተደራዳሪዎቹ ለምን እንዳልተሰጡ እና የድርድር ኮሚቴ ለምን እንዳልተቋቋመ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ በኤጀንሲው ቦርድ በፀደቀው የግዥ መመሪያ ክፍል 6 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 10.3 መሠረት ከአንድ አቅራቢ የተፈጸመ ግዥ ነው ቢሉም ግዥው የመንግሥት ግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51 እና 52 ላይ በደነገገው መልኩ የተፈጸመ ስላልሆነ መልሱን አልተቀበልነውም፡፡

66. በመንግሥት የግዥ አዋጁ 649/2001 አንቀጽ 51፣ 52/2 እና በግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 25.9 እና 25.10 ላይ እንደተገለጸው የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ በመምረጥ ዋጋን ጨምሮ ድርድር ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ድርድር ሳይደረግ እና ለተደራዳሪ ወገኖች የአትኩረተ-ነጥቦች ሳይሰጥ የሚፈጸም ግዥ ለግለሰብ

ውሳኔ የተጋለጠ አሠራር እንዲኖር በማድረግ የአሠራር ክፍተት በመፍጠር የመንግስትና የህዝብ ገንዘብን ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡

**በከፍተኛ ገንዘብ የተፈጸሙ ግዥዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ሁኔታ በመረጃ መረብ (ድረ ገጽ) ላይ መቀመጡን በተመለከተ፤**

67. በከፍተኛ ገንዘብ የተፈጸሙ ግዥዎችን የጨረታ ማስታወቂያና ከአሸናፊ አቅራቢ ጋር የተፈረሙ ውሎችን በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በመድኃኒት ፈንድ እና አቅርቦት ኤጀንሲ የመረጃ ቋት(ድረ ገጽ) ላይ እንዲቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ግዥ የተፈጸመበት ገንዘብ፤ የጨረታው ውጤት፤ እንደዚሁም ውሉ እና ሌሎችም ማስረጃዎች በኤጀንሲው እና በግዥ ኤጀንሲ የመረጃ ድረ ገጽ ላይ እንዲቀመጡ አልተደረገም፡፡

69. ይህንንም በተመለከተ ቀደም ሲል የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲም ሁኔታው ለሚቀጥለው ጊዜ እንዲስተካከል በኦዲት ሪፖርቱ የገለጸ ቢሆንም በሪፖርቱ መሰረትም የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

70. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ሰነዱ ለምን በሁለቱ ኤጀንሲዎች የመረጃ መረብ ላይ እንዳልተቀመጡ ተጠይቀው ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገጽ ላይም እየተጫነ ይገኛል በማለት በነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ቢሉም መረጃዎቹ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ ገጽ ላይ ሊገኙ ባለመቻላቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

71. በህግ በተቀመጠው ሰነዶቹን በመረጃ መረብ አለማስቀመጥ ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ግዥዎች ግልጽነትን አጠያያቂ የሚያደርገው እና እያንዳንዱ ተወዳዳሪም ሆነ ማንኛውም አካል የሚፈልገውን መረጃ በትክክለኛው ጊዜና ቦታ ለማግኘት እንዳይቻል የሚያደርግ ነው፡፡

**በጥራት ጉድለት ስለተመለሱ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት ማስረጃዎቹ መድረሱን መተመለከተ፤**

72. የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለአቅራቢዎቹ እንዲመለሱ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተመላሽ የተደረጉ መድኃኒቶች እና

የህክምና መሳሪያዎች ዝርዝር ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን መመለሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲደርሰው ሊደረግ ይገባል፡፡

73. ይሁን እንጂ የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች እንዲመለሱ ሲደረጉ መመለሳቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለቁጥጥር ባለስልጣኑ እንዲደርሰው የማይደረግ ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለኢትዮጵያ የምግብ፤ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንና ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ባለሥልጣኑም የጥራት ጉድለት ሲያገኝ እንዲመለሱ በደብዳቤ ለኤጀንሲው ከማሳወቅ ውጭ ስለመመለሱ ክትትል የማያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

74. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው ማንኛውም መድኃኒትና የህክምና መገልገያ ከሀገር ውጭ ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚገዛ ሆነ በእርዳታም የተገኘ የመግቢያ ፈቃድ ጥራቱን አረጋግጦ የሚሰጠውና የጥራት ጉድለት መኖሩን አረጋግጦ እንዲመለስ የሚወስነው የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፡፡ ወደ ውጭ በጥራት ጉድለት በሚመለስበት ጊዜ ተቆጣጣሪው አካል ራሱ በማረጋገጥ እንዲወጣ ያደርጋል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ የተገዙ መድኃኒቶች በጥራት ጉድለት በሚመለስበት ጊዜ ተቆጣጣሪው አካል ወደ መጣበት እንዲወጣ ትእዛዝ ይሰጣል እንጂ እንዲወጣ ማድረግ ያለበት ያስመጣው ክፍል ስለሆነ ኤጀንሲው እንዲወጣ አድርጎ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እንዳለበት ባለሥልጣኑ ለኤጀንሲው ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ማረጋገጥ ስለተቻለ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

75. የጥራት ጉድለት አለበት ተብሎ እንዲመለስ ወይንም እዚሁ አገር ውስጥ እንዲወገድ ትዕዛዝ የተሰጠበት መድኃኒት በትክክለኛው መንገድ መመለሱ ወይንም መወገዱ የማይረጋገጥ ከሆነ በምትኩ ጥራቱን የጠበቀ መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች እንዳይመጣ ወይንም የተከፈለውን ገንዘብ ተመላሽ ሳይደረግ በሙስናና በህገወጥ መንገድ አገር ውስጥ ገበያ ላይ የሚውልበት ዕድል የሚከፍትና የህዝብ እና የመንግሥት ገንዘብ የአለአግባብ እንዲጠፋ በር ይከፍታል፡፡

## የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ፤

76. የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ጥናት ሊከናወን ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ የአገሪቱን የወደፊት ፍላጎት የሚሳይ ጥናት ኤጀንሲው ያላጠና መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

78. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ጥናት አጥንተናል ብለው ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም ጥናት ተብሎ የቀረበው የመድኃኒት ስርጭትና አጠቃቀምን በሚመለከት የተከናወነ ሰርቬይ እንጂ የመድኃኒት ፍላጎትን አስመልክቶ የተጠና ጥናት ስላልሆነ ተጠንቷል ተብሎ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

79. የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሆነ በጥናት ተመስርቶ የተደገፈ ካልሆነ በዘርፉ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሆነ የግዥን ስትራቴጂዊ በሆነ መልኩ ማቀድን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ለኤጀንሲው ግዥን አስመልክቶ የሚሰጡትን ማሻሻያዎች ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

80. በኤጀንሲው የግዥ አፈጻጸምን አስመልክቶ የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኦዲት አድርጎ በሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

81. የ2006 በጀት ዓመት በማንኛውም የግዥ ዘዴ የተፈጸሙ ግዥዎችን አስመልክቶ ከአንድ አቅራቢ የብር 9,939,536.91፣ በዋጋ ማቅረቢያ ብር 69,581,974.47፣ በውስን ጨረታ 6,971,893,023.44 በድምሩ 7,051,414,534.82 መጠን ያላቸው ግዥዎች መፈጸሙን የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ19/01/2007 ከላከው የኦዲት ሪፖርት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ ስለመወሰዱ መረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ ለኦዲቱ ባለመቅረቡ እርምጃ ስለመወሰዱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

82. ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ በተሰጠው መልስ ከኦዲት ግኝቱ አስተያየት ጋር ለማጣጣም ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ አብዛኛው ግዥ በግልጽ ጨረታ እየተፈጸመ ይገኛል ቢሉም በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በ2007 እና 2008

በተመሳሳይ ሁኔታ ግዥዎች እየተከናወኑ የቀጠሉ መሆኑን የሚያሳዩ በመሆናቸው የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

83. ይህ አስተያየት የተሰጠው ለወደፊት በሚፈጸሙ ግዥዎች ላይ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም እርማት እንዲደረግ በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ አለመውሰድ ተደጋጋሚ ግዥዎችን ከአዋጅና ከመመሪያ ውጭ በመፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲባክን እና ለብልሹ አሰራርም በር ይከፍታል፡፡

**በጨረታ ላይ የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የጨረታን ውጤት በደብዳቤ መገለጹን በተመለከተ፤**

84. በጨረታ ላይ የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የጨረታን ውጤት በጨረታ ለተወዳደሩ አቅራቢዎች ለራሳቸው ወይም ለወኪሎቻቸው በደብዳቤ እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ ማስረጃዎቹ በኢሜል እንደሚላኩና ለመድረሱ ማረጋገጫ አለመኖሩ የግዥ ኤጀንሲ ኦዲት ሪፖርት እና የፌዴራል የሥነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ኮሚሽን በኤጀንሲው ላይ ያከናወነው የጥናት ሪፖርት ያሳያል፡፡

86. ኮሚሽኑ በሰጠው አስተያየት መሰረት ለማስተካከል የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ በኤጀንሲው ድረገጽ www.pfsa.gov.et መመልከት እንደሚቻል የገለጹ ቢሆንም የተፈለገው ማስረጃ በድህረ ገጽላይ ካለመገኘቱም በላይ በፌዴራል የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተሰጠው አሰተያየት መረጃው በመረጃ መረብ እንዲለቀቅ ሳይሆን በቀጥታ ለተወዳዳሪዎቹ በደብዳቤ እንዲሰጥ ስለሆነ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

87. ሁሉም ተወዳደሪዎች ውጤቱን ሌሎች ተወዳዳሪዎች በጽሁፍ እንዲያውቁት አለመደረጉ በወቅቱ ቅሬታ ወይንም ሌሎች አስተያየቶች ለማቅረብ እንዳይችሉ ከማድረጉም የኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ግዥዎች ሂደት ግልጽነት የጎደለው አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## 2.2 በቀረበው ፍላጎትና ትእዛዝ መሰረት ከውጭ አገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲገዛላቸው ለጠየቁት አካላት መሰራጨታቸውን በተመለከተ፤

**መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለጤና ተቋማት በወቅቱና በጠየቁት መጠን መድረሱን በተመለከተ፤**

88. በየጊዜው እንዲገዛላቸው በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የሚጠየቁ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለጤና ተቋማት በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና መጠይቅ ከቀረበላቸው አዲስ አበባ የሚገኙ ሆስፒታሎች ከሰጡት መልስና ካቀረቡት ማሰረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በአመቱ መጀመሪያ ቀደም ብለው የሚፈልጉትን መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ ፍላጎታቸውን ለኤጀንሲ ቢያሳውቁም ኤጀንሲው ከቀረቡት የፍላጎት ማሳወቂያ ዝርዝር ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ ሊሰጣቸው የሚችለው 30 ከመቶ ብቻ ያህሉን ብቻ እንደሆነ ኤጀንሲው ከሚሰጣቸው የክምችት መጠን ማሳወቂያ እና ከቀረበላቸው መጠይቅ ለመረዳት ተችሎአል፡፡

90. በተጨማሪም ለሆሰፒታሎች አገልግሎት የመጡ መሳሪያዎች የመለዋወጫና የኬሚካል እጥረት ችግር ስለአለባቸው መሣሪያዎቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ በናሙና ከታዩት ሆሰፒታሎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት ተችሎአል፡፡ እንዲሁም ሆስፒታሎቹ ከሚጠይቋቸው መድኃኒቶች ውስጥ ከ2005-2888 ድረስ 986 አይነት የተለያዩ መድኃኒቶች ኤጀንሲው በመጋዘኑ ያለመኖሩን በማረጋገጥ ማቅረብ እንደማይችል በሰንጠረዥ ለሆስፒታሎቹ ከላከው ዝርዝር ለመረዳት ተችሎአል፡፡ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ካቀረቡት ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው በሚፈልጉትና በጠየቁት መሰረት መድኃኒቶች በበቂ ሁኔታ የማይሰጣቸውና አልፎ አልፎም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተቃረበ መድኃኒቶች እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

91. በኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 15/2 የመንግሥት ጤና ተቋማት በወቅቱና በጠየቁት መጠን መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች እንዲደርሳቸው ባለመደረጉ ወይም በራሳቸው መፍትሔ እንዲፈልጉ ኤጀንሲው ድጋፍ ባለማድረጉ ከ2005-2007 ዓ.ም ባለው በጀት ዓመት አዲስ አበባ ከሚገኙት ሆስፒታሎች በናሙና ከታዩት፣

- አ.አ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ፤ የብር 13,681,122.00
- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፤ የብር10,131,830.12፤
- የአገር መከላከያ ሚ/ር፤ የብር 45,199,910.8፤
- የፌዴራል ፖሊስ፤የብር 15,097,626.37
- የዘውዲቱ የብር 1,100,170.96፤
- ጋንዲ መታሰቢያ፤ የብር1,698,378.00
- ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የብር 18,495,260.12

በድምሩ የብር 105,404,299.37 (አንድ መቶ አምስት ሚልዮን አራት መቶ አራት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ37/100) መድኃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች ከኤጀንሲው ውጭ ከግል አስመጪ ድርጅቶች የገዙ መሆኑ ታውቋል፡፡ (አባሪ ስድስት)

92. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ለየጤና ተቋማቱ አስቀድመው በጠየቁት የግዥ ፍላጎት መሰረት መድኃኒቱ ተገዝቶ እንዲደርሳቸው ያልተደረገበትን ምክንያት ተጠይቀው የተጠቀሱት ሆስፒታሎች ከውጭ መድኃኒት በሚገዙበት ጊዜ በኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደተገለጸው መድኃኒቶቹ በኤጀንሲው ውስጥ አለመኖራቸውን የሚገልጽ የማረጋገጫ ወረቀት እንዲኖር ይጠበቃል፣ ሆስፒታሎቹ ይህን አሟልተው ገዝተዋል ብለን እንገምታለን በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የግዥ ዕቅዳቸውን አቅርበው ለነበሩት ሆስፒታሎች መድኃኒቶች በወቅቱ ለምን እንዳልተገዛላቸው ምላሽ ስላልሰጡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

93. ኤጀንሲው ጤና ተቋማቱ የሚፈልጉትን መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በወቅቱ ገዝቶ አለማቅረቡ ተጠቃሚው ህብረተሰብን አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ የሚዳርግ እና የጤና ተቋማቱንም ከዕቅድ ውጭ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲያወጡ ያደርጋቸዋል፡፡

**የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

94. የኤጀንሲው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የተገዙ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በማጓጓዝም ሆነ በማከማቸት ሂደት ወይንም በማንኛውም ምክንያት ብልሽት እንዳይደርስበት ሊጠበቅ ይገባል፡፡ተገዝተውም የሚመጡ መድኃኒቶች እና የህክምና መሳሪያዎች የጥራት ፍተሻ ከተከናወነላቸው በኋላ ወደ ኤጀንሲው መጋዘን ሊገቡ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የጥራት ፍተሻቸው ተጠናቆ እንዲነሱ ትእዛዝ ከተሰጠባቸው ኤጀንሲው መድኃኒቶቹንና መሳሪያዎቹን ሁሉም መሟላት የሚገባቸው ፎርማሊቲዎች ከተሟሉ በኋላ በወቅቱ ባለመረከቡ ከሰባ ስድስት (76) ቀናት በላይ ከተራገፉበት ቦታ ሳይነሱ ያለመጠለያ በዝናብና በጸሀይ በመበላሸታቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑና የገንዘብ መጠናቸው ያልታወቀ በርካታ መድኃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በየመጋዘኑ መኖራቸው በናሙና ከተወሰዱ ባለስልጣኑ ለኤጀንሲው ከላካቸው ደብዳቤዎች፣ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመጋዘን ጉብኝት እንደዚሁም ለመጋዘን ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. በናሙና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው አምራቾች ለመረዳት እንደተቻለው መድኃኒቶችን አምርተው በተያዘላቸው የማስረከቢያ የጊዜ ገደብ ለኤጀንሲው ለማስረከብ ሲፈልጉ ኤጀንሲው በወቅቱ የማይረከባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. ለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው አዳዲሶቹ መጋዘኖች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የኤጀንሲው ማከማቸት አቅም ውስን በመሆኑና የሀገር ውስጥ አምራቾችም በውሉ የማቅረቢያ ጊዜ ሠሌዳ መሠረት የማያቀርቡበት ሁኔታ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በወቅቱ ባለመቅረባቸው ከውጭ በሚገቡት መድኃኒቶች ቦታው ስለሚያዝ ነበር ችግሩ የተፈጠረው፡፡ ይህን ችግር በቋሚነት ለመፍታት ከአምራቾቹ ጋር በቅርበት እየተሠራ ሲሆን አዳዲስ መጋዘኖች ሥራ በመጀመራቸው ችግሩ እየተቀረፈ ይገኛል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ላይ ገልጸዋል፡፡

99. በከፍተኛ ወጪ የሚገዙ መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ከተገዙ በኋላ በፍጥነት ኤጀንሲው ተርክቧቸው ወደ መጋዘኖቹ ካላስገባ እና ለተገዛላቸው አካላት እንዲሰራጩ ካላደረገ መድኃኒቶቹ እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎቹ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በቶሎ በመበላሸት ለብክነት ሊያጋልጡ ከመቻሉም በላይ ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ የሚያባክን እና የመድኃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈባቸው (EXPIRED) መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በተመለከተ፤

100. በኤጀንሲው ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሳያልፍ ለተገዙላቸው የጤና ተቋማት በመሰራጨት ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ሥራ ላይ ሳይውሉ በየበጀት ዓመቱ የተወገዱ መድኃኒቶች የተገዙበትና ሥራ ላይ ያልዋሉበት ምክንያት አጠቃላይ የብክነት መጠን በገንዘብ እየተሰላ በየጊዜው እንዲተነተን ሊደረግ ይገባል፡፡

101. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለሚገዛቸው መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ከጤና ተቋማት በተሰበሰበው ፍላጎት መሰረት የግዥ እቅድ በማውጣት ግዥን መፈጸም ብሎም የገዛቸውን በወቅቱ ማከፋፈል ሲገባው ይህ ባለመሆኑ በከፍተኛ ግንዘብ የተገዙ በኤጀንሲው በዋናው ግቢ እና በሌሎች መጋዘኖች ውስጥ

- አ.አ በሚገኙ የተለያዩ የኤጀንሲው መጋዘኖች በ28/09/06 ከማናጅመንት አስወጋጅ ኮሚቴ በቀረበ ሪፖርት ለማን እና መቼ እንደተገዙ መረጃቸው ያልቀረበ የብር 256,701,046.00 (ሁለት መቶ ሀምሳ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አንድ ሺህ አርባ ስድስት ብር) የሚያወጣ መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች፤
- ከአዳማ ቅርንጫፍ በ26/05/07 በተጻፈ ደብዳቤ እንደተገለጸው የጥራት ችግር ለባቸው የተባሉ ብር 34,863,848 (ሰላሳ አራት ሚሊየን ስምንት መቶ ስልሳ ሦስት ሺ ስምንት መቶ አርባ ስምንት) የሚያወጡ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች፤
- በ2005-2007 ዓ.ም.ከቅርንጫፎች በቀረበ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መሰረት፤ ባህር ዳር ቅርንጫፍ ብር 71,372,697.00፤ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ብር

17,387,474.24፤ ጅማ ቅርንጫፍ ብር 38,528,315.04፣ መቀሌ ቅርንጫፍ ብር 13,979,155.54፣ ሀዋሳ ቅርንጫፍ ብር 26,576,756.01፣ ነቀምት ቅርንጫፍ ብር 11,250,979.12፣ ጎንደር ቅርንጫፍ ብር 7,988,702.96፣ ነገሌ ቦረና ቅርንጫፍ ብር 4,318,389.17፣ አዳማ ቅርንጫፍ ብር 50,752,837.67፣ ደሴ ቅርንጫፍ 20,021,973.13፤ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ 16,091,745.39

በድምሩ 569,833,919.27 (አምስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሚሊየን ስምንት መቶ ሰላሳ ሦስት ሺ ዘጠኝ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ 27/100) የሚያወጣ የአገልግሎት (የመጠቀሚያ) ጊዜያቸው ያለፈባቸው (EXPIRED) መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ መኖሩ ታውቋል፡፡ (አባሪ ሰባት) የአገልግሎት (የመጠቀሚያ) ጊዜው ያለፈበት (EXPIRED) መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ኬሚካሎችም ጭምር አገልግሎት ከሚሰጡ መድኃኒቶች ጋር አብሮ በመጋዘን ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

102. መድኃኒቶቹ እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎቹ በመጀመሪያ ለማን እና ለምን እንደተገዙ፣ እንዲሁም በወቅቱ ለተጠቃሚዎቹ ያልተሰራጩበትን ምክንያት በተመለከተ ተጠይቀው የመድኃኒቶች ብክነት መንስዔ ለግዥ ሲቀርብ ታሳቢ የተደረጉት ሁኔታዎች በመድኃኒቱ አጠቃቀም ትግበራ ወቅት መለያየት፣ መድኃኒቶቹ ተገዝተው በመሰራጨት ላይ እያሉ በዓለም ጤና ድርጅት ለህክምና እንዳይውሉ በመደረጉና በሌላ መድኃኒት በመተካታቸው፣ ከጤና ተቋማት የሚገኘው የመድኃኒት ፍጆታ መረጃ የተሟላ አለመሆንና ለመደበኛ በጀት መድኃኒቶች ግዥ በጤና ተቋማት በቂ በጀት አለመያዝ፣ በተላላፊ በሽታዎች ተኝተው ይታከማሉ ተብለው የተገመተው ህሙማን መጠን በከፍተኛ መጠን መቀነስ ምክንያት ነዉ፡፡

103. ለጤና ፕሮግራሞች ከውጭ በእርዳታ ከመጡ መድኃኒቶችም ውስጥ በከፊል ጥቅም ላይ ሳይውሉ የሚቀሩበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ለወረርሽኝ መከላከያና መቆጣጠሪያ ተገዝተዉ ለምሣል ወባ፤ ተቅማጥ፤ የወፍ ጉንፋን ፤ኢቦላ…ወዘተ በሽታዎች) ወርርሽኝ ሳይከሰት ስቀርና ሲከሰትም በዝቅተኛ ሁኔታ ሲሆን መድኃኒቶቹና ህክምና መገልገያዎቹ ጥቅም ለይ ሳይወሉ የመቅረት እድል ይኖራል፡፡ ወረርሽኙ ተከስቶ በቂ የመድሃኒት ቅድመ-ዝግጅት ባለመኖር ሊያሳድር ከሚችለው ተፅዕኖዎች (በህዝብ ጤና፤ ማህበራዊና ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖዎች) አንፃር ግን በቂ ክምችት መያዝ የግድ በሚል ምክንያት የተገዙ በመሆናቸው ነው በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት

አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በየአመቱ የግዥ ዕቅድ ሲታቀድ በእጅ ላይ ያለ መድኃኒት ክምችትን ከግምት በማስገባት ማቀድ ይቻል ስለነበረ፣ እንዲሁም የአለም ጤና ድርጅት የትኞቹን መድኃኒቶች ሥራ ላይ እንዳይውሉ የወሰነበት ማስረጃም ሆነ ጊዜ የሚገልጽ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ መቀበል ያስቸግራል፡፡ መድኃኒቶቹ ለምን እስከአሁን እንዳልተወገዱ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

104. መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ  መሳሪዎች ተገዝተው ከመጡ በኋላ ለየጤና ተቋማት ሳይሰራጩ የአገልግሎት (የመጠቀሚያ) ጊዜያቸው በመጋዘን ውስጥ እያሉ የሚያልፍባቸው (EXPIRED) ከሆነ ኤጀንሲው ግዥን በፍላጎት ላይ ተመስርቶ በማቀድ የሚያከናውን መሆኑን ጥያቄ ውስጥ የሚስያገባ፣ ዕቅዱ በመጋዘን ውስጥ ያሉትን እንደማያገናዝብ እና መድኃኒቶቹን እና የህክምና መገልገያ  መሣሪያዎቹን ለመግዛት የዋለው ከፍተኛ የህዝብ እና የመንግሥ"ት ሀብትን የአለአግባብ እንዲባክን ከማድረጉም በላይ አላስፈላጊ ለሆነ የመጋዘን ኪራይ ኤጀንሲው ወጪ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

## ክፍል ሦስት

### መደምደሚያ

105. የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተግኝተዋል፡፡

- ኤጀንሲው ያዘጋጀው የሥራ አመራር ቦርድ የሰጠውን ማስተካከያ ሳያካትት የግዥ መመሪያውን እየተጠቀመ መሆኑ፣ የተዘጋጀው መመሪያ የአገሪቱን የግዥ አዋጅ በመቃረን ለየግዥ ዘዴ ስልቱ የገንዘብ ጣራ መጠን እንዲቀመጥ ያላደረገ መሆኑ፤
- የኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ ዕቅድ የማይዘጋጅ እና የሚቀርቡ ጥያቄዎች በበጀት መደገፋቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- በኤጀንሲው የሚገዙ መድኃኒቶች እና የሕክምና መሣሪያዎች ግዥ የሚከናወንበት የግዥ ስልት ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ የተከናወኑ ግዢዎች የተመረጡበት ምክንያትና የግዢውን ሂደት የሚያሳይ መረጃ አለመቅረቡ ፤
- የፕሮግራም መድኃኒቶች ትንበያና የግዥ እቅድ አዘገጃጀትን ለማከናወን የቴክኒክ ቡድን ያልተቋቋመ መሆኑና የሚገዙት መድኃኒቶች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የማይሰራጩ መሆኑ፤
- የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ከእቅድ ውጪ ለሚፈጸም አስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች ግዥ የሚያገለግል መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- በመንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያ ግዥ ያልተፈጸመ መሆኑ፤
- መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ በግዥ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና መመሪያ ሳይኖር የተገዛ መድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች እየተሰራጩላቸው መሆኑ ፤
- ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸሙ ግዥዎች የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑና የአትኩረት- ነጥቦች ተዘጋጅተው ለተደራዳሪዎች ያልተሰጡ መሆኑ፤
- በከፍተኛ ገንዘብ የተፈጸሙ ግዥዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ሁኔታ በኤጀንሲው እና በግዥ ኤጀንሲ የመረጃ መረብ (ድረ ገጽ) ላይ የማይቀመጥ መሆኑ፤

- በጥራት ጉድለት ስለተመለሱ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ማስረጃ እንዲደርስ የማይደረግ መሆኑ፤
- የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ጥናት ያልተከናወነ መሆኑ፤
- በኤጀንሲውን የግዥ አፈጻጸምን ገምግመው ግበረ መልስ የሰጡ አካላት በሰጡት የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ኤጀንሲው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለጤና ተቋማት በወቅቱ የማይሰጣቸው መሆኑ፤
- የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- (የመጠቀሚያ) ጊዜው ያለፈበት (EXPIRED) መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች መኖራቸው፣

ታውቋል፡፡

ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የተመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

106. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያ ግዥዎችን በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡-

- ኤጀንሲው የአዘጋጀውን መመሪያ በመንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ መሰረት፣ በሥራ አመራር ቦርዱ የተሰጠውን የማስተካከያ ሃሳብ በማካተት እንዲሁም በመንግሥት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ለእያንዳንዱ የግዥ ስልት የገንዘብ ተመን ጣራ በማስቀመጥ የግዥ መመሪያውን በአፋጣኝ በመከለስ እና ተግባራዊ በማድረግ የሕዝብ እና የመንግሥት ሀብትን ከምዝበራና ህገወጥነትን የሚከላከል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በየዓመቱ ለሚያከናውናቸው የመደበኛም ሆነ የፕሮግራም የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የግዥ እቅድ ለማሰባሰብ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ፍላጎታቸውን ሊያሰባስብ እና በእርግጥ እንዲገዛላቸው ለሚፈልጉት መድኃኒትም ሆነ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች መግዣ የተመደበ በጀት እንዳላቸው በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ከየባለድርሻ አካላቱ ያሰባሰበውን የግዥ ፍላጎት በመተንተን እና በመጋዘኖቹ ውስጥ ያለውን የመድኃኒት ክምችቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት እና ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማጸደቅ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የግዥ ዕቅዱን ሲዘጋጅ የትኞቹ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በየትኛው የግዥ ስልት (በግልጽ ጨረታ፣ ውስን ጨረታ፣ ከአንድ አቅራቢ፣በዋጋ ማወዳደሪያ) ግዥዎች ሊከናወኑ እንደሚገባ ስልቱ የተመረጠበትን ምክንያት ጭምር በሚገልጽ መልኩ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ መሰረት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡የተከናወኑትም ግዥዎችም የግዥ ሂደቶቹን የሚያሳዩ መረጃዎች ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡
- በፕሮግራም በጀት የሚገዙ መድኃኒቶች ልክ የኤች.አይ.ቪ. (HIV) እና ለወባ መድኃኒቶች ግዥ ላይ እንደተጀመረው፣ ለሌሎቹም (የቤተሰብ ምጣኔ፣የሳንባ ነቀርሳ

(የቲቢና) የሥጋ ደዌ (ሌፕረሲ) እንዲሁም ሌሎች የፕሮግራም መድኃኒቶች) ትንበያና የግዥ እቅድ፣ በጀት አዘገጃጀትን ለማከናወን የቴክኒክ ቡድን እንዲቋቋም ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተገዙትም መድኃኒቶች በወቅቱ ለየጤና ተቋማቱ በማሰራጨት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በመደበኛ ሆነ በፕሮግራም በጀቶች የሚፈጽማቸውን የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ ምዝገባ በጊዜ፤ በአይነት፤ በመጠን፤ በገንዘብ መጠን፣ ከየትኛው በጀት እና ለእነማን እንደተገዛ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ በመዘርዘር ምዝገባ ሊያከናውን ይህንንም በመረጃ አያያዝ ቴክኖሎጂ ሊደግፈው ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው አስቸኳይ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት ለሚያከናውናቸው ከእቅድ ውጪ ለሚፈጸም ማናቸውም ግዥዎች የሚመሩበት አስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ መመሪያ በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል አጸድቆ ሥራ ላይ ሊያውልና በዕቅድ ውስጥ ተካተው መገዛት ያለባቸውን መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ በማዘጋጀት ህገወጥ የሆኑ አሰራሮችን ሊከላከል ይገባዋል፡፡
- ኤጀንሲው የራሱን የግዥ መመሪያ በመንግሥት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ለመግዛት የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሰረት ያደረገ ግዥ ማከናወን አለበት፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው መንግሥታዊ ላልሆኑ ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ በግዥ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ በማውጣት በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ አድርጎ ፍላጎታቸውን አመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ በማድረግ ህገወጥ አሰራርን ሊያስወግድ፡፡
- ኤጀንሲው በግዥ አዋጁ እና መመሪያው በተፈቀደው መሰረት ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚፈጸም ግዥ ሲያጋጥመው የድርድር ማድረጊያ አትኩረተ- ነጥቦች በግዥ አዋጁ አንቀጽ 52/2 መሰረት ሊያዘጋጅ እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በማጸደቅ ለተደራዳሪ ወገኖች ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም መ/ቤቱን ወክሎ በአትኩረተ-ነጥቦቹ መሰረት የሚደራደር የዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ በማቋቋም የዋጋ ድርድሩን ሊያካሂድ እና የህዝብና የመንግሥትን ፍላጎትና ጥቅም ሊያስጠብቅ ይገባል፡፡

- በከፍተኛ ገንዘብ የተፈጸሙ ግዥዎችን የጨረታ ማስታወቂያና ከአሸናፊ አቅራቢ ጋር የተፈረሙ ውሎችን ልክ እንደተከናወኑ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በመድኃኒት ፈንድ እና አቅርቦት ኤጀንሲ የመረጃ መረብ (ድረ ገጽ) ላይ እንዲቀመጡ ሊደረግ እና መረጃዎቹ የሚመለከታቸው አካላት እንዲያገኙት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የአገር ውስጥ አምራቾችም ሆነ ከውጭ አገር የተገዙት ጥራት ጉድለት የተገኘባቸው መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች እንዲመለሱ ሲደረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን መመለሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲደርሰው በማድርግ መድኃኒቶቹ እና የህክምና መሣሪያዎቹ በህገወጥ መንገድ አገር ውስጥ ገበያ ላይ እንዳይሸጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በተመለሱት መድኃኒቶች ምትክም ጥራቱን የጠበቀ መድኃኒት ወይም የህክምና መገልገያ መሣሪያ መተካቱ ወይም በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ ካለ ተመላሽ መደረጉን ሊከታተል እና የህዝብ ሀብት ያለአግባብ እንዳይባክን ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የአገሪቱን የመድኃኒት ፈንድ የሚያስተዳድር እንደመሆኑ መጠን ካለው የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችና ግዥ አፈጻጸም በመነሳት የአገሪቱ የወደፊት የመድኃኒት ፍላጎት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ጥናት በማከናወን በዘርፉ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንትም ሆነ የመድኃኒት እና የህክምና ፍላጎት ሊያከናወን እና የወደፊቱ አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበት መንግሥትን ሊያማክር ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ላይ የተለያየ ግምገማ በማከናወን የማሻሻያ ሀሳብ እና ግብረ መልስ ሲሰጠው (ለምሳሌ በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በፌዴራል የሥነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን) በሚሰጠው አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- በየጊዜው እንዲገዛላቸው በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የሚጠየቁ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለየጤና ተቋማት በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው ማድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም በብዛት የሚፈለጉ እና መሰረታዊ የሚባሉ መድኃኒቶች አነስተኛ የክምችት መጠን ወጥቶላቸው ለየጤና ተቋማቱ በወቅቱ በማስራጨት ተቋማቱ የሚከናውኑትን የቁጥ ቁጥ ግዥ ሊያስቀር እና

ህብረተሰቡንም የታዘዙለትን መድኃኒቶቹን ለማግኘት ተጨማሪ ወጪ እንዳያወጣ ሊያደረግ ይገባል፡፡

- የኤጀንሲው ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የገዛቸውን የመድኃኒት የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ተፈላጊውን ጥራት መሟላታቸው ሲረጋግጥ በፍጥነት ተረክቦ በማጓጓዝም እና ወደ መጋዘኖቹ ሊያስገባ ብሎም መድኃኒቶቹ ለተገዛላቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባዋል፡፡ይህንን በማድረግም ሊከሰት የሚችሉ ከአገልግሎት ውጭ የመሆን አደጋን እና አላስፈላጊ ሆኑ የመጋዘን ወጪዎችን ሊቀንስ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ተገዝተው ሥራ ላይ ሳይውሉ በየበጀት ዓመቱ የተወገዱ መድኃኒቶች የተገዙበት ምክንያት ለማን እና ከየትኛው በጀት እንደተገዙ፣ ለምን ለተገዛላቸው አካላት በወቅቱ ተሰራጭተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያልተደረገበትን ምክንያት፣ አጠቃላይ የብክነት መጠን በገንዘብ እየተሰላ በዝርዝር በማጥናትና በመተንተን ወደፊት ይህ እንዳይደገም የሚያደርግ ሥርዓት ሊዘረጋ እና ውጤቱንም ለቦርዱ እና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

107. በአጠቃላይ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸምን አስመልክቶ ኤጀንሲው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለሚገዛቸው መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ከጤና ተቋማት በተሰበሰበው ፍላጎት መሰረት የግዥ እቅድ ማውጣትና ማጸደቅ፣ እንደዚሁም ግዥ የሚፈጸምበት የግዥ መመሪያ ማውጣትና ማጸደቅ በጸደቀው የግዥ መመሪያ መሰረት የገዛቸውን መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በሚፈለገው መጠን በወቅቱ ለጤና ተቋማት በማከፋፈል ትክክለኛ ምዝገባ ማከናወኑ እና መረጃው ለሚመለከተው አካል መድረሱ፣ የጤና ተቋማት እና የመድኃኒት አምራቾች እና አከፋፋዮች በተቀላጠፈ ሁኔታ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፡፡ ይህም ሥራ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርንም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመድኃኒት ግዥና አቅርቦት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላትን የተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

108. በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች ኤጀንሲው በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በአዋጁ እና

በደንቡ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው መ/ቤቶች፣ ሆስፒታሎች እና የድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ አንድ፡


## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| 1 የመድሐኒትና የሕክምና መሳሪያዎች፣በሚፈለገው ወቅት፣በተመጣጣኝ ዋጋ እናቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤ | 1. ኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ ከጤና ቢሮዎችና ከጤና ተቋማት በየዓመቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ |
| | 2. የሚሰበሰበው ዓመታዊ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያዎች አቅርቦት ጥያቄ በመጠን፣በጊዜና እና በገንዘብ ሊገለጽ ይገባል፡፡ |
| | 3. የሚሰበሰበው የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያዎች አቅርቦት ጥያቄ ዓመታዊ በጀትን የሚያሳይ ሊሆን ይገባል፡፡. |
| | 4. የሚቀርብ የመድኃኒት ፍላጎት ተጠናቅሮ ተተንት እና ተገምግሞ እንዲቀርብ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ኤጀንሲው በቀረበው ፍላጎት መሰረት የመድኃኒት ግዢ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 6. መድኃኒቱ ወይም የሕክምና መሳሪያው በመጋዘን ውስጥ በቂ መጠን መኖሩ እየታወቀ ተጨማሪ ግዥ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 7. በጤና ተቋማት ለሚገኝ ዝቅተኛ(minimum stock level) የመድኃኒት ክምችት መጠን መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 8. በጤና ተቋማት የሚገኙ ዝቅተኛ (minimum stock level) የመድኃኒት ክምችቶችን መጠን የሚቆጣጠር ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል፡፡ |
| | 9. የሚዘጋጀው የግዥ እቅድ በየትኞቹ የግዥ ስልቶች ግዥዎች ሊከናወኑ እንደሚገባ በሚገልጽ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10. የኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች የግዥ በጀት በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡ |
| | 11. የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ግዢ በጀት በትክክል በሥራ ላይ መዋሉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 12. መንግሥታዊ ላልሆነና ለግል የጤና ተቋማት መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያ ለማቅረብ የሚያገለግል መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. ከእቅድ ውጪ ለሚፈጸም አስቸኳይ የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ግዥ መስፈርት ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡ |
| | 14.የአገር ውስጥ የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያ አምራቾችና አቅራቢዎች የማቅረብ አቅማቸው ከታየ በኋላ ለውጭ ሀገር ግዥ ጨረታ እንዲወጣ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15. የሀገር ውስጥ አምራቾች ወይም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ግዥ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| | የተፈጸመባቸውን .መድኃኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎችን ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 16.ኤጀንሲው.ለመድኃኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች ግዥ በሚከፍለው ቅድሚያ ክፍያ መሰረት ምርቱ በወቅቱ እንዲቀርብ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. የመድኃኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች ተገዝተው ሲገቡ ደህንነታቸው ፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 18.በኤጀንሲው ለሚገዙ መድኃኒቶች አነስተኛ የመጠቀሚያ ጊዜ ገደባቸውን የሚገልጽ ስታንዳርድ ሊወጣ ይገባል፡፡ |
| | 19.መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያ ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ጥራትና ብቃትን ለማረጋገጥ የሚረዳ መሳሪያ በየፍተሻ ጣቢያ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 20. ኤጀንሲው ለሚያከናወናቸውበጨረታ የሚወጡ መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ግዥ ዝርዝር መግለጫ(ስፔስፊኬሽን) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 21.ለመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች ግዥ የሚዘጋጁ የጨረታ ሰነዶች እንደ ግዥው አይነት ሊገለጹ የሚገባቸው ሁኔታዎች እና መሰረታዊ ጉዳዮች የተሟሉ መሆኑ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 22.ኤጀንሲው የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎችን ግዥ ለመፈጸም ለሚያወጣው ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሰነድ ሊጠቀም ይገባል፡፡ |
| | 23. የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያ ግዢ ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ፍቃድ ከተሰጣቸው /ፈቃዳቸውን ካታደሰላቸው ድርጅቶች ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 24. የመድኃኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች ግዥ ቀደም ሲል የግዥ ትንበያና አቅም ግንባታ በተነበየው ዋጋ ላይ ተመርኩዞ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 25. የጨረታውን ውጤት በጨረታ ለተወዳደሩ አቅራቢዎች ለራሳቸው ወይም ለወኪሎቻቸው በደብዳቤ እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 26.የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያ ግዥን በሚመለከትኤጀንሲው ጨረታውን ካሸነፊው አካል ጋር መካተት ያበትን ግዴታዎች የያዘ ውል ሊፈራረም ይገባል፡፡ |
| | 27.የኤጀንሲው የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 2.በቀረበው ፍላጎትና ትእዛዝ መሰረት ከውጭ አገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች እና | 28. የመድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች የግዥ ስርዓት የሚመራበት ዘመናዊ የሎጂስቲክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 29. ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የተገዙ መድኃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎችን ኤጀንሲው በወቅቱ ሊረከብ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት |
| --- | --- |
| የሕክምና መሣሪያዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዲገዙላቸው ለጠየቁት አካላት መሰራጨታቸውን ማረጋገ | 30. ኤጀንሲው ማንኛውም በግዥ ወይም በእርዳታ ያገኘውን መድኃኒት ከመረከቡ በፊት የተጠየቀው አይነትና መጠን ያልተበላሸ እና የአገልግሎት ጊዜው ከማለፉ በፊት አገልግሎት ላይ ሊውል እንደሚችል መረጋገጥ አለበት |
| | 31. የግዥ ዕቅድን ለማዘጋጀት በኤጀንሲው መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መድኃኒቶች ክምችት ለማወቅ የሚያግዝ አማካይ ወርሀዊ ፍጆታን፣ የመጠባበቂያ፣ ዝቅተኛና፣ ከፍተኛ መጠን ለማወቅ በስቶክ :ካርድ ላይ ሊመዘገብ ይገባል፡፡ |
| | 32. የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች የግዥና የማጓጓዝ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 33.የተዘጋጀው ዕቅድም አፈጻጸሙ ቢያንስ በየሦስት ወሩ አፈጻጸሙ እንዲገመገም ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 34. ያለፉት ጊዜያት ፍጆታ፣ የአቅርቦት ክፍተት፣በማዕከል መጋዘኖች በክምችት የሚገኝ፣ በጨረታ ሂደት እና በመንገድ ላይ ያለው ክምችት መጠን ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 35. ኤጀንሲው የመድኃኒት ግዥን እና ማጓጓዝን የሚመለከቱ የአፈጻጸም መመሪያዎች አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ |
| | 36. የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና የተበላሹ መድኃኒቶች የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 37. ጥቅም ላይ የማይውሉ ወይም ጌዜ ያለፈባቸውና የተበላሹ መድኃኒቶች አወጋገድ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 38.ተገዝተው ሥራ ላይ ሳይውሉ በየበጀት ዓመቱ የተወገዱ መድኃኒቶች የተገዙበትና ሥራ ላይ ያልዋሉበት ምክንያት አጠቃላይ የብክነት መጠን በገንዘብ እየተለካ ቤጊዜው ሊተነተን ይገባል፡፡ ይገባል፡፡ |
| | 39. የጤና ፕሮገራም መድኃኒቶችን ትንበያና የግዥ እቅድ አዘገጃጀት ለማከናወን የቴክኒክ ቡድን ሊቋቋም ይገባል፡፡ |
| | 40. የተቋቋመው የቴክኒክ ቡድን በየዓመቱ የሦስት ዓመት ፍላጎትና የአንድ ዓመት የግዥ ዕቅድ እንደየፕሮግራሙ ሁኔታ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 41. ኤጅንሲው የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች የግዥ ጥያቄ፣ግዥና አቅርቦት ላይ ሙያዊ የምክር አገልግሎትና ሥልጠና ለጤና ተቋማት ለአምራቾች እና ላቅራቢዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 42.ከሀገር ውስጥ አምራቾች ጋር በየሩብ ዓመቱ የውይይት መደረክ በማዘጋጀት በአቅርቦት አፈጻጻማቸው እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 43. ከውጭ አገር የሚፈጸመውን የመድኃኒትና<br>የህክምና መሳሪያ ግዥ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እንዲቻል የአገር ውስጥ አምራቾች የማምረት አቅማቸው እንዲጎለብት ሊደረግ ይገባል፡፡ |

## አባሪ ሁለት፡ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ ሦስት፡

በ2005፣ 2006 እና 2007 ዓ.ምግዥን ሂደት የሚገልጽ ማስረጃ እና የግዥው መንገድ የተመረጠበት ምክንያት በግልጽ ሳይቀመጥ የተገዙ መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን፤

| ተ.ቁ | የግዥው ዘዴ ዝርዝር | የጨረታው ዓይነት | የ2005 ዓ.ም | የ2006 ዓ.ም | የ2007 ዓ.ም | ጠቅላላ ድምር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በግልጽ ጨረታ () | ከአገር ውስጥ | -- | -- | -- | -- | |
| | | ከአለም አቀፍ | 679,811,380.15 | 392,306,794.00 | 3,296,735,536.21 | **4,368,853,710.36** | |
| 2 | በሁለት ደረጃ ጨረታ() | ከአገር ውስጥ | -- | -- | -- | -- | |
| | | ከአለም አቀፍ | -- | -- | -- | -- | |
| 3 | በመወዳደርያ ሐሳብ() | ከአገር ውስጥ | -- | -- | -- | -- | |
| | | ከአለም አቀፍ | -- | -- | -- | -- | |
| 4 | በውስን ጨረታ () | ከአገር ውስጥ | 1,535,519,974.71 | 830,518,232.00 | 1,827,389,346.73 | **4,193,427,553.44** | |
| | | ከአለም አቀፍ | 2,851,263,301.09 | 3,892,325,708.00 | 430,367,801.27 | **7,173,956,810.36** | |
| 5 | በዋጋ ማቅረብያ | ከአገር ውስጥ | 16,692,937.55 | 4,274,214.00 | 5,521,190.00 | **26,488,341.55** | |
| | | ከአለም አቀፍ | 33,000,275.10 | 16,622,787.00 | 138,544,748.34 | **188,167,810.44** | |
| 6 | ከአንድ አቅራቢ() | ከአገር ውስጥ | 25,733,349.36 | 15,906,074.00 | 796,112.50 | **42,435,535.86** | |
| | | ከአለም አቀፍ | 375,983,582.09 | 178,880,347.00 | 94,919,651.51 | **649,783,580.60** | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | | | | **16,643,113,342.61** | |

## አባሪ አራት፡

## ለግል የጤና ተቋማት የተሰጡት መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን

| ተ.ቁ | የቅርንጫፍ ስም ዝርዝር | ለግል የጤና ተቋማት የተሰጡ መድኃኒቶች | | | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2005 | 2006 | 2007 | |
| 1 | አዲስ አበባ ቅርንጫፍ | -- | -- | -- | -- |
| 2 | አዳማ ቅርንጫፍ | - | 6,175,031.03 | 22,953,123.94 | 29,128,154.97 |
| 3 | ሀዋሳ ቅርንጫፍ | -- | 24,732,449.58 | 38,784,183.40 | 63,516,632.98 |
| 4 | የጅማ ቅርንጫፍ | - | -- | -- | -- |
| 5 | የነቀምት ቅርንጫፍ | 8,518,116.00 | -- | 13,174,041.10 | 21,692,157.10 |
| 6 | ደሴ ቅርንጫፍ | -- | -- | 8,306,590.10 | 8,306,590.10 |
| 7 | ባህርዳር ቅርንጫፍ | 18,025,105.00 | 27,162,395.00 | 20,478,101.00 | 65,665,601.00 |
| 8 | ነገሌ ቦረና | -- | -- | 9,322,186.96 | 9,322,186.96 |
| 9 | የድሬዳዋ ቅርንጫፍ | -- | -- | 19,291,604.29 | 19,291,604.29 |
| 10 | ጎንደር ቅርንጭፍ | 9,368,725.55 | -- | 10,984,742.51 | 20,353,468.06 |
| 11 | መቐለ ቅርንጫ | -- | -- | 8,100,550.26 | 8,100,550.26 |
| | ጠቅላላ ዋጋ | | | | **245,376,945.72** |

## አባሪ አምስት

**በናሙና ከታዩ አራት ቀጥታ ግዥዎች (ከአንድ አቅራቢ) ያለ ዋጋ ተደራዳሪ ኮሚቴ የተፈጸሙ መድኃኒትና ህክምና መገልገያ ግዥዎች ዝርዝር**

| አሸናፊ አቅራቢ | የጨረታ ቁጥር | ጠቅላላ ዋጋ (በብር) |
|---|---|---|
| 1.Novartis Famycare limited Mission pharma | PFSA6/DT/MDG/KIDENY TRANSPLANT/RDF/PH/05/15 | 18,967,303.46 |
| 2.INBIOS | PFSA6/DT/MOH/KALAZAR/RTK/34/15 | 630,105.55 |
| 3.EPHARM | PFSA6/DT/RDF/PH/21/13 | 247,000.00 |
| 4.ALCON | PFSA6/DT/RDF/PH/01/14 | 1,406,281.37 |
| | TOTAL= | 21,250,689.83 |

አባሪ ስድስት

## በአዲስ አበባ የሚገኙ የጤና ተቋማት ከመድኃኒት ፈንድ ውጭ የገዙት መድኃኒት በገንዘብ መጠን

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | የ2005 ዓ.ም | የ2006 ዓ.ም | የ2007 ዓ.ም | ጠቅላላ ድምር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥቁር አንበሳ ስፔሻ/ ሆ/ል | 662,248.00 | 1,162,815.00 | 11,856,059.00 | **13,681,122.00** | |
| 2 | ጳውሎስ ሆስፒታል | 1876657.60 | 2661719.42 | 5593453.10 | **10,131,830.12** | |
| 3 | መከላከያ ሆስፒታል | 13,499,492.57 | 15,497,347.10 | 16,203,071.14 | **45,199,910.8** | |
| 4 | አለርት ሆስፒታል | -- | -- | -- | **--** | |
| 5 | ፖሊስ ሆስፒታል | 4902076.82 | 4151422.28 | 6044127.27 | **15,097,626.37** | |
| 6 | ዘውዲቱ ሆስፒታል | 547,125.00 | 511,149.96 | 1,041,896.00 | **1,100,170.96** | |
| 7 | ጋንዲ ሆስፒታል | 172,609.34 | 972,438.09 | 553,330.57 | **1,698,378.00** | |
| 8 | ሚኒሊክ ሆስፒታል | 6217458.68 | 1149195.65 | 11128605.79 | **18,495,260.12** | |
| 9 | ራስደስታ ሆስፒታል | -- | -- | -- | -- | |
| 10 | የካቲት ሆስፒታል | -- | -- | -- | -- | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | | | **105,404,299.00** | |

## አባሪ ሰባት፡

### በአዲስ አበባና በቅርንጫፍ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያበቃ መድኃኒቶች በገንዘብ መጠን

| ተ.ቁ | የቅርንጫፍ ስም ዝርዝር | የመጠቀምያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒት | | | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2005 | 2006 | 2007 | |
| 1 | አዲስ አበባ | -- | 16,091,745.39 | -- | 16,091,745.39 |
| 2 | አዳማ | 8,464,554.60 | 77,152,131.37 | -- | 85,616,685.67 |
| 3 | ሀዋሳ | -- | 11,824,235.45 | 14,752,520.56 | 26,576,756.01 |
| 4 | ጅማ | -- | 27,932,409.21 | 10,595,905.83 | 38,528,315.04 |
| 5 | ነቀምት | 2,613,606.79 | 6,627,649.06 | 2,493,763.07 | 11,250,979.12 |
| 6 | ደሴ | 7,245,947.72 | 9,704,497.40 | 3,071,528.01 | 20,021,973.13 |
| 7 | ባህርዳር | 7,842,110.00 | 29,576,111.00 | 33,954,476.00 | 71,372,697.00 |
| 8 | ነገሌ ቦረና | -- | 4,318,389.17 | -- | 4,318,389.17 |
| 9 | ድሬዳዋ | -- | 17,387,474.24 | -- | 17,387,474.24 |
| 10 | ጎንደር | 3,215,099.33 | 2,292,930.34 | 2,480,673.29 | 7,988,702.96 |
| 11 | መቐለ | -- | 13,979,155.65 | -- | 13,979,155.65 |
| | ጠቅላላ ዋጋ | | | | **313,132,873.53** |